# ቁንጣንና ጠኔ ክፍል 2
# (ከኮቸናው ቫንኩቨር )

በገዥዎችና በህዝባችን መሃል ያለው ልዩነትና አስተሳሰብ በተለይም የእለት እለት ኑሮን በተመልከተ በነኝህ እጅግ ባስተሳሰብና በአንዋንዋር በተልያዩ መሃል ያለው ልዩነት ቀደምቱ ገድሎ ገዝቶ በፈለገውና እንደፈልገው የመኖርና ቀጣዩ ደግሞ በጠኔና ጣር እንዳይጠፋ  ቤተሰቡንና አራሱን አብልቶ ከዛሬ ሞት ለመዳን የሚያደርገው ትግል መሆኑን እየተመለከትን ነው። የህዝባችን ስለበልቶ መኖሩና በሰላም ገብቶ ስለመውጣቱ እንዲሁም ስለደህንነቱ ከሱ የበለጠ ተመልካችና ጠባቂ አንደሌለው መገንዘብ ከጀመረ ቆይትዋል።ዛሬ ህዝባችን የሉአላዊነት መለያ የሆኑ ምልክቶች አየደበዘዙ በድንበር ያለ ዉዝግብ ሳይሆን በደጁ እየተከሰት የሚያያቸው አዳዲስ ክስተቶች እያስፈሩት መጥተዋል። **ዛሬ ሃገራችን ባለቤትና ተምዋጋች በማጣትዋ ምክንያት ድንበራችን እየጠበበ የሃገራችን ድንበር ከደጃችን ደርስዋል።** ለረጅም ጊዜ ሲያወዛግበን የነበረው የምእራባውያን አቅዋም ከመቸውም ጊዜ ሁሉ ዛሬ ግልፅ የሆነ መሰለኝ። የኢትዮጵያ ህዝብ ነፃነት **የማያስፈልገው** መሆኑን ግልፅ በሆነ ቁዋንቁዋ አስቀምጠዋል። ኀበዝ ልብ ልንል የሚገባን ሰአት አሁን መሰለኝ። ህወሃት ዛሬ የሃገሪቱን ሃብት መጠና አስመጥጦ ታሪክና ጊዜ ወደያዘለት መቃብር ለመጉዋዝ እየመረሸ፡  ሃገራችን ቆርሶ ዛረ በቁዋንቁዋና በባህል ለማይገጥሙን ባእዳን እየሸነሸነ ኢያለ፡/ ኢትዮጵያችን ከጥቂት ጊዜ በህዋላ የይገባኛል ጥያቄ ለማንሳት አረቦችና ሌሎችም በየደጃችን ሰፍረው ለም መረቶቻችን ሲያመክኑ እያየን/ ህዝባችንን በረሃብና በተቻለው ሁሉ ለማጥፋት መንግስትና ማህበርተኞቻቸው ሌት ከቀን ሲባዝኑ እያየን፡/ ህወሃት ህዝብ ተርቦ አንዳች ከማድረግ ግን በካድሬ ምልመላና በምርጫ ዘመቻ እየተጣደፈ እያየን፡/ ለምርጫ የሚያስፈልጉ ንጥሮች ባልተምዋሉበት ነፃ ምርጫ እያለ ሲዘባበትብን እያየን ዛሬም የህወሃት ተስፈኞች ሆነን መላ ከመሻት ግን መላ የሚያፈላልጉ ወገኖቻችንን ጠልፈን ለመጣል ጥድፍያ ላይ እንገኛለን።ዛሬ ምእራባውያን በቻይና መስፋፋት ምክንያት አፍሪካ ውስጥ ስያራምዱት የነበረውን የደሞክራሲ ጥያቄ አፈር አልብሰውታል። ቻይና ለአፍሪካ አምባገነኖች ጥሩ አማራጭ ሆናለች። አፍሪካውያን አምባገነኖች ቀድሞውንም ዴሞክራሲ የሚባል በሽታ አንዳይነሳባቸው መሻታቸውንና ባህሪያቸውን ጠንቅቃ የተረዳችው ቻይና ዛሬ አፍሪካውያን አምባገነኖች ረግጠውና ገለው የመኖር እድል አንዳላቸው በማስገንዘብና ባለሞያዎችና ገዳዮችን በማሰልጠን በልዋጩ ሃብት እያጋበሱ ይገኛሉ። ህዝባችን በልቶ የሚያድረው በማጣቱ በባህሉና በወጉ ነውር ብሎ ሲያወግዛቸው የነበሩ ሁሉ ባህርያት ተላመዳቸው። በ13ና ብ14 አመት አድሜ ያሉ ሴት አህቶቻችን አንደህፃንነታቸው በሃገራቸው ከወገናቸው ጋር መቦረቁ ቀርቶ ቤተሰቦቻቸውን አብልቶ ለማሳደር በማለት በባአድ ሃገር አስከሬናቸው አንደ ዉሻ በየቦዩ ይጣላል።ሴት አህቶቻችን አንደማንኛዉም ሸቀጥ ወደ ዉጭ እየተቸበቸቡ ይገኛሉ። አሁን ህዝባችን ለማውራት በሚዘገንን ሁነታ ላይ ባለበት በዚህ ሁኔታ ቀድሞውንም ለህዝቡ ደንታ የሌለው መንግስት ነኝ ተብየው ከዚህም ከዚያም በሚያግበሰብሰው የውጭ አርዳታ የካድሬ መንጋ በማምረት እየተጣደፈ ይገኛል። ምናልባትም አጅግ የሚያስጨንቀው አስከምርጫ ተብየው ሰአት ህወሃት ስለምርጫው አንጅ የህዝቡን ረሃብ ለማርገብ ምንም አርምጃ ካለመውሰዱም ሌላ ህዝቡን ለመመገብ የተሰለፉ የእርዳታ ሰጭ ድርጅቶችን ከሚንቀሳቀሱበት አካባቢ እያሳደደ ከሃገር እንዲወጡ የሚያደርገው ዘመቻ ነው። ሰሞኑን በመገናኛ ብዙሃን በሰፊው ሲነዛ የቆየው የምርጫ ስነምግባር ስምምነት የስንቶቻችንን ቀልብ አንደሳበ ባይገባኝም ግን የሂደትንና የታሪክን መደጋገም ከዚህ ቀደም ከተስተዋሉ የፈራረሱ ስምምነቶችንና የአፍራሽን ባህርይ በመገምገም ምን ያህል ስለመግዋዙ ለመገመት ነብይ መሆንን የሚጠይቅ ባይሆንም ግን ሰዎች በራሳቸው አለም ዙርያ ያመኑበትንና አፈፃጸሙን በማስተዋል ብስለታቸውንና ብልህነታቸውን አንደገና በድጋሚ ሊያሳዩን ታጥቀው መነሳታቸውን ሲነግሩን በብልህነትና በጨዋነት

-2-

ልናስተውል በድጋሚ አድል ስለሰጡን ግባቸው ግብ ይሆናል ብለን ባንሞኝም ግን አሁንም ቢሆን የመጨረሻ መፍትሄ ይሆናል ብለን ያመንበትን አቅዋማችንን እያራመድን በማስተዋል የምንግዋዝበትን እድል ማግኘታችን መዘንጋት የለበትም። ዛሬ አስከ ዛሬ ሲያስጨንቀን ግራ ሲያጋባን  የነበረው እንቆቅልሽ ከመቸውም ጊዜ ግልፅ እየሆነ መጥቶዋል። እስከዛረ በአለም አቀፍ ደረጃ ስናካሂድ የነበረው ሰላማዊ ጉዞ ሰሚ አጥቶ ህዝባችን በግፍና በግፈኞች እየተሰቃየ እንዲኖር የሆነበት ምክንያት ምእራባውያኑ በግልፅ አሳዩን። በተዘዋዋሪም በሰሞኑ በአፍጋኒስታን የታየው ድራማና የምርጫ ቅጥፈትና የምእራብያውያኑ ሰይጣናዊ አቅዋም እኛም አይናችንን እንድንከፍት ሲያደርግ የፓለስታይኑ መሪ ለህዝቡ

ጭብጥ የሆነ ለውጥ ሊያስገኝ ባለመቻሉ በታሪክ ተወቃሽ እንደሚያደርገው በመገምት ግዜ የመግዣ መሳርያና መሆን እንደማይፈልግና በስልጣን መቆየት እንደማይፈልግ በመግልፅ ሰሞኑን መርጫ ማካሄድ እንደሚፈልግ መግለፁ ደግሞ ለህወሃት አጃቢዎች መልካም ትምህርት የሚሰጥ ይመስላል። ምእራብያውያኑ የመከራችን ጊዜ ማብቅያ ገና እንደሆነ በግልፅ የነገሩን መሰለኝ። እንግዲህ ይህንን መስማትና ማየት የሚችል ዜጋ ሁሉ ሊያስተውል የሚገባው ጉዳይ ነው። እዚህ ላይ ይህ የአለምና የሃገር ዉስጥ ሁነታ የትግል ስልታችንን አበክረን ደግመን ደጋግመን እንድናጤን የሚጋብዘን ይመስላል። ያለንበት አጣብቂኝ ከራሳችን ዉጭ ለራሳችንና ለውገናችን ማንም እንደሌለው መገንዘብ ብቻ ሳይሆን የህዝባችንን በረሃብ ቸነፈር ግምት ዉስጥ በማስገባት የኢትዮጵያ ህዝብ ረሃብ የህወሃት ዉጤት መሆኑን ተገንዝበን ፈጥነን ህዝባችንን ከረሃብ ለማውጣት የሚደረገውን ግን ህወሃትን ላይ ያነጣጠረትግልን የሚጋብዝ ጊዜ መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።ማንኛውም ህዝባችንን ከባርነትና ከዘረኞች ግፍ የማላቀቅ ትግል ዛሬ በህዝባችን ላይ የተጋረጠውን ረሃብ ብሎም የምናየውን እልቂት የመቀነስ ብሎም የማጥፋት ትግል መሆኑን ማመን አያስቸግርም።በሃግራችን ስላለው የፖለቲካ ቀውስና ከዚህ ጋር በተያያዘ የተከሰተውን ችግር ለማስወገድ ምንም ይሁን ምን ስለህጋዊነቱ የሚያጠያይቅ አይሆንም። የምንግዋዝበትን ጉዞና ጎዳና የሚቀድልንና የሚፈቅድልን ከኛው ዉጭ ማንም ሊሆን እንደማይችል ማወቅ ብልህነት ነው። ህግና ስርአት በሌለበት ህግ በመይከበርበትና የዜጎች መብት በተረገጠበት ሁኔታ ህግን ለማስከበር የሚደረግ ማንኛውም ትግል ህጋዊነቱ ግልፅ ነው። **ህግን ያወጣ ሃይል ህግን ሲጥስ ህግ ይከበር ብሎ መጠየቅን የመሰለ የሞራል ጥያቄ የለም። ጥቂቶቹ በነፃነትና በተድላ የሚኖሩባትና ጥቂቱ በልቶና ጠጥቶ የሚንደላቀቅባት ሃገር ግን ህዝባችን ጎረቤቱን በየእለቱ እየቀበረ የነገ መቀበሪያዉን የሚምስባት ኢትዮጵያ ሆና እንዳትቀር ተግተን መጣር ያለብን ይመስላል።**

<u>ይህን የተቀደሰ ትግል የዚህን ትውልድ ማንነት ጥያቄ ውስጥ የሚያስገባ የዚህ ትውልድ ብቻ ግዴታ ሆኖ እንዲቀርና ለተተኪው ትውልድ የማይተላለፍ ውርስ እንዳይሆን አበክረን መስራት ይጠበቅብናል።</u> በሰለጠነው ሃገር መልካም ስነምግባር ቅርስና ታሪክ እንጂ መከራና ግፍ ለትውልድ እንዳያልፍ ሌት ተቀን ይሰራበታል የምናየውም ነው። ከእንቅልፍ እየባነንን ዛሬ ይህ ነው የማይባል ችግር ያልፈጠሩና የጋራችን የሆነውን ጠላት እየታገሉ የሚገኙ ግለሰቦችንና ድርጅቶችን ማውገዙን ትተን የጋራ ግንባር መፍጠር የግዜው ጥሪት ነው። እስከ ዛሬ የጎዳንን አሉባልታና ጥላቻና የግል ዝናን የማካበቱን ጥረት አስወግደን ኢትዮጵያ ሃገራችንን የምናስቀድምበትን ሁኔታ መፍጠር ይኖርብናል። የህዝባችን ተስፋ የሌለው ኑሮ ማብቃት አለበት። ረሃብ ጊዜ አይሰጥምና!! የነሱም ጠግቦ የህዝባችንም ተርቦ የመኖር ሁኔታ የማብቅያው ጊዜ ሩቅ አይሆንም። እንደ ቃልቻ ያግዋራብን የአይጋው አንበሳና ግብረአበሮቹም ለሰሩት ስራ ፍትህን ያገኛሉ። ኢትዮጵያችንም እንደገና ታብባለች!!!

*ፈጣሪ ይርዳን*